ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON  M6H - 1L8
**Tel./ Fax:  416 - 516 1244**

# ማሳሰቢያ

## በቶሮንቶና አካባቢው ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

ኦክቶበር 1 ቀን 2007 ዓ.ም እራሱን "ቅንጅት ለሰብዓዊ መብትና ለዲሞክራሲ በቶሮንቶ" ወይም "ቅንጅት ካናዳ ምክር ቤት" እያለ የሚጠራው ቡድን "ልሳነ ቅንጅት" (Volume 1:No.1) በሚል በራሪ ጽሑፍ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ማርያም ካቴድራል ቅጥር ግቢ የመስቀል በዓል አከባበር ላይ በትኗል፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ ይህ ቡድን የቅንጅትን ትግል የሐሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛትና ሥም በማጥፋት እንዲያዳክም አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃነ መዋና ዶ/ር ሞገስ ገብረማርያም ያቂቂሙት መሆኑን ከዚህ በፊት ባወጣነው ማሳሰቢያ አስታውቀናል፡፡ በተለይም ይህ ቡድን የቅንጅትን ሥምና አርማ ለመጠቀም እውቅናና ፈቃድ ያልሰጠነው መሆኑን መግለጻችን ይታወቃል፡፡ ይህንንም ጉዳይ አስመልክቶ የቅንጅት ስምና አርማ መጠቀም በፍጥነት እንዲያቆም በሕግ ጠበቃ አማካኝነት ተልኮለት፤ ስላላቆመ ድርጅታችን የሕግ ክስ መሥርቶ መልስ በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡

የቅንጅት መሪዎች እሥር ላይ በነበሩበት ጊዜ በነ መለስ ዜናዊ ልዩ ተልዕኮ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ በውጭ አገር የቅንጅት ድጋፍ ለመከፋፈልና ለማዳከም ድጋፍ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ወይም ለማፍረስ ያም ካልሆነ በቅንጅት ሥም ተለጣፊ ድርጅቶች በማቋቋም ህብረተሰቡን ግራ የማጋባት ተግባራት ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡

ቶሮንቶም ድርሻውን ለመጀመሪያ ጊዜ ተለጣፊ ቡድን አግኝቷል፡፡  በአቶ ዩሱፍ ኡመር መሪነት ቅንጅት ነኝ ብሎ በጥቂት አጀብና ሆያ ሆዬ የተቋቋመው ተለጣፊ ቡድን የከፋፋይነት መርዝ የሚረጩ ህብረተሰቡን ግራ የሚያጋቡ ተባራሪ ወረቀቶችን በተለያዩ <u>ጊዜያት</u> ሲበትን ቆይቷል፡፡ እዩኝ፣ ዕወቁኝ፣ አድንቁኝ፣ ተአምር ሠሪ ነኝ እያለ ያደነቁረናል፡፡ የነ አየለ ጫሚሶን ፈለግ በመከተል የተቋቋመው ይኸው አቶ ዩሱፍ ኡመር የሚመራው ቡድን ሙሉ ጊዜውን በዌብ ሳይቶች በሚለጠፍና በፓል ቶክ በሚተላለፍ ነጭ ውሸት በድርጅታችን ሥራ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ሞክሯል፡፡ ሆኖም በቅንጅት ድጋፍ ላይ ሌላ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት ማቋቋሙ ለምን አስፈለገ እያለ ዘወትር የሚጠይቀው የኮሚኒቲያችን አብዛኛው ነዋሪ ሚስጥሩን ተረድቶታል፡፡ ቁም ነገሩ ይህ ሆኖ ሳለ ይህ በሕገወጥ መንገድ የቅንጅትን ትግል ለማዳከም የተቂቂመ ቡድን የቅንጅትን አመራር ልዑካን ለመቀበል በዝግጅት ላይ መሆኑን ለሕዝብ አስታውቂል፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ የልዑካኑ ቡድን የቅንጅቱን ፕሬዚዳንትና የቡድኑን መሪ ሳይዝ ብቻውን የሚጓዘው፤ ብዙ ሕዝብ ሕይወቱን የከፈለበትን፣ መከራ ያየበትን፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የታሰሩበትን፣ የተሰቃዩበትንና የተሰደዱበትን ትግል አኮላሽቶ ከወያኔ ጋር ሥውር ድርድር አካሂዶ የሕዝብና የአገር ጥቅም ሳይሆን የራሱን ጥቅም ለማግኘት በመሯሯጥ ላይ ነው፡፡ ይህ ምሕረት የማይደረግለት ክሕደት መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ይህንን አፈንጋጭ ቡድን ካለመሪውና ቆራጡ የኢትዮጵያ ጀግና ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ውጭ ወደ ቶሮንቶና ሌሎች የካናዳ ከተሞች መጥቶ ሕዝብ የማነጋገር ሥልጣኑም ሆነ የሞራል ብቃት የለውም፡፡ ስለሆነም ከፋፋይ ተግባሩን እንቃወማለ ፡፡ አንቀበለውምም፡፡ በቶሮንቶና አካባቢው የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህንን ተረድቶ እንዳይታለል አጥብቀን ማሳሰብ እንወዳለን፡፡

በቶሮንቶና አካባቢው የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ላለው ትግል የተቻለውን የገንዘብ፣ የሞራል፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቲል፡፡ ያገርና የሕዝብ ጥሪ ተቀብሎ እስካሁን ላደረገው ጠቅላላ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ምስጋና ደግመን ልናቀርብ እንወዳለን፡፡ እስካሁን ላደረገውም አስተዋፅጽኦ ከትግሉ መሪ ከክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ምስጋና መቀበልና ጠቅላላ ውይይትም ማድረግ መብቱ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ስለዚህም የቅንጅት ፕሬዚዳንት ሕክምናቸው እንዳለቀና በአሜሪካ የሚያደርጉት ተመሳሳይ ፕሮግራም እንዳለቀ ወደ ካናዳ እንደሚመጡና እንደሚገናኟችሁ አረጋግጠውልናል፡፡ ቀኑና ሰዓቱን ወደፊት በዝርዝር እናቀርባለን፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ባታላዮች ወጥመድ ውስጥ ባለማወቅ እንዳትገቡ እናሳስባለን፡፡

---

*Office Address:*     4 Westmoreland Ave. Toronto, Ontario M6H 2Z7     *(Bloor St.W. & West of Dovercourt)*